# የክተት የመጀመሪያ እርምጃ

የክተት አስፈላጊነት እየተዘነጋ መጥቶ እንደሆነ፣ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከእስር ቤት እንድትፈታ ያደረገችው ኑዛዜ ነው ብሎ የበተነው ኢሰብአዊ ፈጠራ ያስታውሰናል። እርግጥ ያንን ጽፈው ሲያቀርቡላት ፈርማው ከሆነ የብረት አንካሴ በእሳት አግለው ወደ አጉል ቦታ ቢያነጣጥሩባት ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን አያደርጉም የሚል ካለ ማንነታቸውን የማያውቅ ነው።

ስለ ክተት ጽንሰ ሐሳብ በአጭሩ ለመከለስ ያህል፣ ዓላማው "ጊዜው እስኪደርስ፣ የፓርቲን እርምጃ አቆይቶ የፖለቲካ መስኩን መደልደል" ነው። ያለፉት የምርጫ ሂደቶች እንዳሳዩት፣ ሂደቱን የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር እስከተቆጣጠረው ድረስ "አባቱ ዳኛ፣ አባቱ ቀማኛ" ይሆናል። መንግሥቱ እንደትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር ሰራቂ፣ ዘራፊ ከሆነ፣ የሚገባው እርምጃ ቀማኛውን በመጣበት መንገድ በመጣበት ዘዴ ማስወገድና የሕዝብ መንግሥት ማቋቋም ብቻ ነው። የሕዝብ መንግሥት ማቋቋም እንዴት እንደሆነ እናውቃለን፤ የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር የመጣበትን መንገድና የመጣበትን ዘዴንም እናውቃለን። የክተት ዓላማ ያንን ዕውቀታችንን በሥራ ላይ እንድናውለው ጥሪና የእርምጃ ንድፍ ነው።

ጥሪውንና ንድፉን ለማቅረብ ያነሳሳኝ "የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ግምባር አገሪቷን የሚቀልድባት በአንድነት ስላልተቋቋምነው ነው፤ አንድ መሆን አለብን" የሚለው ድምፅ ከድምፅ ሳያልፍ ማየቴና ከድምፅ እንዲያልፍ የሚያደርግ ሐሳብ አለማየቴ ነው። ይኸንን ስል ድርጅቶች አብሮ ለመሥራት ያደረጉትንና የሚያደርጉትን ጥረት ሳላከብር በመቅረት አይደለም። **የክተት** ጥሪ ኢትዮጵያ ውስጥ በአካል የሚታገሉትን ነፃ አውጪዎች የድዮስጶራው ኢትዮጵያውያን እንዲረዷቸው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለመፍጠር ነው። ይህ ሐሳብ ኢትዮጵያ ውስጥ በአካል የሚታገል አካል መኖርን ይጠይቃል። ያ አካል አሁን አለ ወይ? ጥሪው ከላይ እንዳልኩት፣ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች (ፓርቲዎች) "ጊዜው እስኪደርስ፣ የፓርቲን ሂደት አቆይቶ የፖለቲካ መስኩን ለመደልደል ወደዚያ አካልነት እንዲለወጡ ነው።" ካልተለወጡ ለተለመደው እንቅስቃሴ ጠቃሚ ድጋፍ ያገኙ አይመስለኝም። እነሱ ባይለወጡም ሌላ አካል መነሣቱ አይቀርም። የጀግኖችና የነፃነት ወዳጆች ሀገር ነፃ አውጪ ግምባር እንደሚወጣባት አልጠራጠርም። ለማንኛውም የድዮስጶራው ሕዝብ መካተት የነፃ አውጪ ግምባርን መፈጠር ያጣድፈዋል። ክተት በወር ሃያ ሃያ ዶላር የሚያዋጡ ሁለት ሺ አባላት ቢኖሩት የቱን ያህል ኀይል እንደሚሆን እናስብ። ቢያንስ ቢያንስ ከአንድ ሺ አባላት ካልተመዘግቡ አንድነትን የሚፈልጉ ብዙዎች ላለመሆናቸው መረጃ ይሆነናል።

ለክተት የመጀመሪያ እርምጃ ሁለት ነገሮች ተዘጋጅተዋል። ክተቶቹን ሁሉ የሚያገለግል ቢያበዙት የሚብዛ አንድ ድረ ገጽ ተዘጋጅቷል፤ ለያንዳንዱ ክተት ከራሱ ድረ ገጹ የላይኞቹ ሁለት ማዕዘኖች ላይ የሚለጠፉ ሁለት አርማዎች (logo) ተቀርጸውለታል። በግራ ማዕዘን የሚለጠፈው አርማ "ክተት ድዮስጶራ" ይላል፤ መላ ድዮስጶራው አንድ መሆናችንን ያመለክታል። በቀኝ ማዕዘን የሚለጠፈው አርማ አህጉራዊ ነው፤ እንደየ አህጉሩ፣ "ክተት አሜሪካ"፣ "ክተት ካናዳ"፣ "ክተት አውሮፓ"፣ "ክተት አፍሪካ"፣ "ክተት አውስትራሊያ" ይላል። መልኮቹን www.ethiokitet.org ግብቶ ማየት ይቻላል። እውነት አንድነትን የምንፈልግ ከሆነ፣ በየአህጉሩ ካሉት ኢትዮጵያውያን ጥቂቶች ተጠራርተው ድረ ገጻቸውን ከማባዢያው ወስደው ያላንዳች ወጪ ማዘጋጀት ይችላሉ፤ ይጠበቅባቸዋልም።

አባላት ማስመዝገቢያውና መሪዎቻችንን መጠቆሚያው ሰለዳ እየተዘጋጀ ነው። www.ethiokitet.org የተባለውን ድረ ገጻችንን እየጎበኛችሁ ተከታተሉን።